# ደምብ

MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS
**የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ**

**ተዛማጅ ምንጮች:** JPD፣ JPD-RA፣ JPD-RB፣ JPD-RC
**ኃላፊነት ያለው ጽ/ቤት:** Office of the School System Medical Officer; Office of School Support and Well-being

## ለተማሪዎች የመድሐኒት አሰጣጥ

I. **ዓላማ**

አስፈላጊ ሲሆን ለተማሪዎች በትምህርት ሰአት መድሀኒት የመስጠት አሠራር መመሪያ ለመመሥረት ነው

II. **ዳራ**

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) እና የሞንትጎመሪ ካውንቲ የጤና እና ሰብአዊ አገልግሎት ዲፓርትመንት (DHHS)፣ ከት/ቤት የጤና አገልግሎት (SHS) ጋር በመሆን በተገቢ ሁኔታ የመድኃኒቶች አያያዝ እና አጠቃቀም ደንቦችን እና የአሠራር ሂደቶችን በጋራ በማዘጋጀት ይተገብራሉ። የዚህ ደንብ ተግባራዊነት MCPS፣ SHS፣ ወላጆች/አሳዳጊዎች፣ተማሪዎች እና መድኃኒት ለማዘዝ ፈቃድ ባለው የጤና ባለሙያ መካከል በትብብር ይከናወናል።

III. **ትርጉም**

A. መድኃኒት የማዘዝ ፈቃድ ያላቸው ማለት:- በሜሪላንድ ህግ መሰረት ለግለሰቦች የጤና እንክብካቤ ለመስጠት እና መድሃኒት ለማዘዝ ፍቃድ ያላቸው ሰዎች ማለት ነው። እነዚህም ፈቃድ ያላቸው የጤና ባለሙያዎች፣ ሠርተፊኬት ያላቸው የተመዘገቡ ነርስ ሐኪሞች፣ ሠርተፊኬት ያላቸው ነርስ-አዋላጆች፣ ፈቃድ ያላቸው ፔዲያትሪስቶች፣ ፈቃድ ያላቸው ረዳት ሐኪሞች፣ እና ፈቃድ ያላቸው የጥርስ ሐኪሞችን ያካትታል።

B. ቁጥጥር የሚደረግባቸው መድኃኒቶች የሚያካትቱት:- በዚህ ብቻ የሚገደብ ሳይሆን፥ አበረታች ንጥረ ነገሮችን (ትኩረት አልባነትን የሚያነቃቃ መድሀኒት/ሃይፐርአክቲቪቲ ዲስኦርደር (ADHD) ጭምር) እንዲሁም ድብርትን ለመከላከል የሚወሰዱ መድኃኒቶች፣ ናርኮቲክ እና አንዳንድ አደንዛዥ ዕፆች ናቸው። በድንገት የሚጥል በሽታ መድሀኒቶች፣ቁጥጥር የሚደረግባቸው ንጥረ ነገሮች ተብለው ቢመደቡም፣ እንደ ሌሎች ቁጥጥር የሚደረግባቸው መድኃኒቶች ተመሳሳይ የአያያዝ መስፈርቶችን መጠበቅ ግዴታ አይሆንም፣ ምክንያቱም ሰክሽን IV.E ላይ እንደተገለጸው የሚጥል በሽታ በሚነሳበት ጊዜ ለተማሪ በፍጥነት መድሃኒቱን ለመስጠት ዝግጁ መሆን አለባቸው።

C. ከዕፅዋት የተቀመሙ መድኃኒቶች የተለያዩ ዕፅዋቶችና ከዕፅዋት የተገኙ መድኃኒቶች ናቸው።

D. በትንሽ በትንሽ መድሀኒት በመስጠት በሽታን የማከም ዘዴ/የሆሚዮፓቲክ መድኃኒቶች ሆሚዮፓቲክ ተብለው የተሰየሙ እና በሆሚዮፓቲክ ፋርማሲዎች የተዘጋጁ የመድኃኒት ምርቶች በዩናይትድ ስቴትስ ሆሚዮፓቲክ ፋርማኮፖኢያ/Homeopathic Pharmacopoeia of the United States ተብለው የተገለጹት አሠራሮች በዩናይትድ ስቴትስ የምግብ እና የመድኃኒት አስተዳደር ይፋዊ የማኑፋክቸሪንግ መመሪያ መሠረት የተዘጋጀ ነው።

E. Over-the-counter (OTC) medications/በቀጥታ ከመደርደሪያ የሚገዙ መድሃኒቶች ማለት፡- በዩናይትድ ስቴትስ ያለ ሃኪም ትእዛዝ ሊገዙ የሚችሉ መድሃኒቶች ናቸው።

F. በሐኪም የሚታዘዙ መድኃኒቶች ፈቃድ ባላቸው የህክምና በለሙያዎች መታዘዝ ያለባቸው መድኃኒቶች ናቸው።

IV. የአሠራር ሂደት

A. SHS ወይም በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሰራተኞች ለተማሪዎች የመድሀኒት አሰጣጥ

1. በህክምና ምክንያት አስፈላጊ ካልሆነ በስተቀር በትምህርት ቀን ለተማሪዎች መድሃኒት መስጠትን MCPS እና SHS አያበረታቱም።

2. DHHS ፖሊሲ ላይ እንደተደነገገው SHS የሥራ ባልደረቦች በትምህርት ሠዓት የሚገኙ ከሆነ፣ በትምህርት ቤት የጤና አገልግሎት መመሪያ/ማኑዋል መሠረት በትምህርት ቤት ሰአት መድሃኒት ይሰጣሉ።

3. DHHS የትምህርት ቤት የጤና አገልግሎት መመሪያ መሠረት የ SHS ሰራተኞች በማይገኙበት ጊዜ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሰራተኞች መድሃኒት እንዲሰጡ መመደብ የርእሰመምህሩ/የተወካዩ ኃላፊነት ነው።

4. ርእሰ መምህሩ/ተወካይ ከትምህርት ቤቱ የማህበረሰብ ጤና ነርስ (SCHN) ጋር ጊዜውን በጠበቀ መልኩ ይሰራሉ፣ የተመደቡት የ SHS ሰራተኞች በማይኖሩበት ጊዜ ለተማሪዎች መድሃኒት መስጠት እንዲችሉ የሚመደቡት ሠራተኞች ተገቢውን ስልጠና ማግኘታቸውን SHS ያረጋግጣል።

5. የ MCPS ሰራተኞች በመደበኛነት ለተማሪዎች መድሃኒት እንዲሰጡ በሚጠበቅባቸው ሁኔታ፣ የስቴት ህግ በሚጠይቀው መሰረት በመድሃኒት ቴክኒሻንነት ሠርተፊኬት ማግኘት አለባቸው። ሰራተኞች መድሀኒት ለመስጠት በቴክኒሻንነት የሠለጠኑ እና የእውቅና ማረጋገጫው/ሠርተፊኬታቸው ወቅታዊ መሆን ስላለበት የሞንትጎመሪ ካውንቲ የጤና እና የሰብአዊ አገልግሎት ዲፓርትመንት ስልጠና ይሰጣል።

6. MCPS፣ የሰለጠኑ የጤና ባለሙያዎች ወይም የመድኃኒት ቴክኒሻኖች የምስክር ወረቀት ያላቸው ሠራተኞች ብቻ ጥንቃቄ የሚያሻቸው መድኃኒቶችን ወይም የሕክምና መሣሪያዎችን (ለምሳሌ፡- ቴርሞሜትር) የመሳሰሉ ጥንቃቄ የሚያሻው የሕክምና እርዳታ ማከናወን ይችላሉ።

B. ተማሪዎች መድሃኒት በራሳቸው የሚወስዱበት ሁኔታ

ያደጉ እና ብቃት ያላቸው ተማሪዎች በጤና ባለሙያ ከታዘዘላቸው እና SCHN ከተፈቀደላቸው የአስም መድኃኒት መንፍያ፣ ኤፒነፊሪን አውቶ-ኢንጀክተርስ ወይም ኢንሱሊን (inhalers, epinephrine auto-injectors, or insulin) የመሳሰሉ አንዳንድ መድሃኒቶችን በራሳቸው መውሰድ/መርፌ መወጋት ይችላሉ።

1. MCPS ቅፅ 525-13፣ በሀኪም የታዘዙ መድሀኒቶችን የመስጠት ፈቃድ፣ መሞላት እና መድሃኒቱን ባዘዘው ፈቃድ ያለው/ያላት የጤና ባለሙያ መፈረም አለበት፣ ይሄውም ተማሪው/ዋ መድሀኒቱን መያዝ እና በግል-መውሰድ እንደሚችል/እንደምትችል የሚገልጽ መሆን አለበት። (እባክዎ MCPS ቅጽ 525-14 ሲሞሉ አናፊላክሲስ ምርመራ ላለው/ላላት ተማሪ የድንገተኛ ጊዜ እንክብካቤ ለማድረግ፣ በራስ-የሚወጋ epinephrine ስለሚፈቀድበት ሁኔታ ደንብ JPD-RB ውስጥ ያሉትን አሠራሮች ያስተውሉ።)

2. ተማሪው(ዋ) መድሃኒት በራሱ(ሷ) የመውሰድ ብቃት እንዳለው/እንዳላት SCHN መገምገም እና ማጽደቅ/መፍቀድ አለበት።

3. ተማሪዎች ቁጥጥር የሚደረግባቸው መድኃኒቶችን/ንጥረነገሮችን በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ንብረት ውስጥ በፍጹም ይዘው መገኘት ወይም እራሳቸው መውሰድ አይችሉም።

4. ተማሪዎች በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ንብረት ውስጥ አደንዛዥ እፅ/ካናቢስ በፍፁም ማጨስ፣ ይዞ መገኘት፣ ወይም በራሳቸው ለመውሰድ አይችሉም–

    a) የሜሪላንድ ስቴት የትምህርት ዲፓርትመንት መመሪያ ተማሪ በራሱ እንዲወስድ/እንድትወስድ ወይም በማንኛውም መልኩ የህክምና አደንዛዥ ካናቢስ እንዳይዝ/እንዳትይዝ የሚከለክል ከመሆኑም በላይ፣

    b) የሜሪላንድ ህግ፣ የትኛውንም የህክምና አደንዛዥ እፅ/ካናቢስ አጠቃቀምን በትምህርት ቤት ንብረት ውስጥ መጠቀም ወይም ማጨስ ይከለክላል።

5. አውቶማቲክ-መወጊያ ያለው ኤፒንፊሪን (epinephrine) አወሳሰድ MCPS ደንብ JPD-RB፣ አናፍላክሲስ (Anaphylaxis) ላጋጠማቸው ተማሪዎች የድንገተኛ ጊዜ እንክብካቤ በዝርዝር ተገልጿል።

6. MCPS ደንብ JPD-RC ላይ እንደተገለጸው፣ ኦፒዮይድ ከመጠን በላይ የመውሰድ ምልክቶች ላጋጠማቸው ተማሪዎች የድንገተኛ ህክምና እንክብካቤ፣MCPS ንብረት ውስጥ እና በት/ቤት በሚደገፉ እንቅስቃሴዎች ይዘው የሚገኙ ተማሪዎች ናሎክሶን ይዘው በመገኘታቸው ምክንያት ብቻ የቅጣት እርምጃ አይወሰድባቸውም።

C. የመድሀኒት መታሸግ እና መሰየም ሂደት

ሁሉም የታዘዙ መድሀኒቶች በማስቀመጫ ውስጥ ከፋርማሲ ስማቸው ጋር መቅረብ አለባቸው። ትክክለኛው የታዘዘ መድሀኒት ማስቀመጫ በፋርማሲስት በተገቢ መንገድ መሰየም አለበት፣ ይሄም በሜሪላንድ ህግ መሰረት ነው። የፋርማሲ ስያሜው የሚከተሉትንን ማካተት አለበት፡-

1. የመድኃኒቱ ስም

2. የአከፋፋዩ ስም እና አድራሻ

3. መድሀኒቱ የታዘዘበት ቀን፣ ወይም መድሀኒቱ ድጋሚ የተሞላበት ቀን እና የሚያበቃበት ቀን

4. መድኃኒት ለማዘዝ የተፈቀደለት ሰው ስም

5. የታካሚው ስም

6. ማንኛውም የአጠቃቀም መመሪያዎች (ለምሳሌ፡- ለምን ያህል ጊዜ መወሰድ እንዳለበት፣ መሰጠት ያለበት የመድኃኒት መጠን እና የአሰጣጡ ሁኔታ)

D. OTC መድሃኒት እና በሰው ላይ ችግር ሊያስከትሉ የሚችሉ መድኃኒቶችን ለበሽተኛ በትንሹ እየሰጡ የማከም ዘዴ/የሆሚዮፓቲክ እና የእፅዋት መድሃኒቶች የሚተገበሩት በሐኪም በታዘዘ የመድሃኒት

አሰጣቃቀም መሰረት ነው፣ ለዚህም የወላጅ/አሳዳጊ የጽሁፍ ፍቃድ እና ፈቃድ ያለው የሃኪም ትእዛዝ በጽሑፍ መሰጠት አለበት።

1. OTC መድሀኒት በአምራቹ ትክክለኛ ማሸጊያ ውስጥ መሆን አለበት፣ ይኼውም የመድኃኒቱ ስም እና የድህንነት መጠበቂያ እሽጉ ሳይከፈት መሆን አለበት።

2. ሆሚዮፓቲክ ወይም ከእፅዋት የተዘጋጀ መድሀኒት OTC ምርት ከሆነ፣ መድሃኒቱ በአምራቹ የመጀመሪያ ማሸጊያ ውስጥ መሆን አለበት፣ መለያው እና የእሽጉ ማህተም ሳይበላሽ መጠበቅ አለበት።

E. የመድሀኒት አቀማመጥ/አያያዝ

1. ግለሰብ ተማሪዎች ለመያዝ እና በግል- የመውሰድ ፈቃድ ከተሰጣቸው መድሀኒቶች በስተቀር፣ ሁሉም መድሀኒቶች በሚቆለፍ ማስቀመጫ ውስጥ መቀመጥ አለባቸው፣ ከዚህ በታች በተገለጸው መሰረት SCHN መድሀኒቶቹን ለመስጠት ፈቃድ ያላቸው ግለሰቦች ብቻ ሊያገኟቸው ይገባል።

2. ሁሉም መድሃኒቶች ውጤታማነታቸውን ለመጠበቅ እና መድሃኒቶችን ለመስጠት ያልተፈቀደላቸው ሰዎች በማይደርሱበት የተለየ ቦታ ተቆልፎ መቀመጥ አለባቸው።

3. ለመድሀኒት ማስቀመጫነት የሚያገለግሉ ማቀዝቀዣዎች ተቆልፈው እና አጠቃቀማቸው መድሃኒት ለማስቀመጥ ብቻ የተመደቡ መሆን አለባቸው።

4. ቁጥጥር የሚደረግባቸው መድኃኒት ነክ ንጥረ ነገሮች፣ከላይ እንደተገለፀው ነፃ ከተባሉት በስተቀር፣በድርብ ቁልፍ ተቆልፈው መቀመጥ አለባቸው (ማለትም፡- በተቆለፈ ሣጥን ውስጥ ሆኖ፣ በተቆለፈ የጠረጴዛ መሳቢያ ወይም የፋይል ካቢኔት ውስጥ መቀመጥ አለባቸው) ። ቁጥጥር የሚደረግባቸው መድኃኒት ነክ ንጥረ-ነገሮች ዝርዝር በየወሩ እና ቁጥጥር የሚደረግባቸው የመድኃኒት ንጥረ-ነገር አቅርቦት ወደ ት/ቤት በሚመጣበት በማንኛውም ወቅት ኢንቨንተሪ መደረግ አለበት።

    a) የድንገተኛ ጊዜ እና ሌሎች የሚጥል በሽታ መድኃኒቶች በጤና ክፍል ውስጥ በተቆለፈ ሳጥን ወይም ካቢኔ ውስጥ መድኃኒቱን መቼ መሰጠት እንዳለበት መመሪያዎችን ያካተተ የተፈረመ የሐኪም ትዕዛዝ አንድላይ መቀመጥ አለበት።

    b) ከተማሪ ጋር አብረው መሄድ የሚያስፈልጋቸው መድሃኒቶች (ለምሳሌ፡- በመስክ ጉዞ ወቅት) ከተማሪው ጋር ሳይሆን ኃላፊነት ያለው፣ የሰለጠነ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሰራተኛ ጋር መቀመጥ አለባቸው።

5. ሁሉም መድሃኒቶች፣ የአገልግሎት ጊዜያቸው ካለፈበት አንድ ሳምንት በኋላ፣ ወይም በትምህርት አመቱ መጨረሻ ላይ መድሃኒቱ መቋረጡን ለሚመለከታቸው ተገለጾላቸው በወላጅ/አሳዳጊ ወይም እነርሱ በሚወክሉት ሌላ አዋቂ ሰው አማካይነት ከትምህርት ቤቱ መወገድ አለባቸው።

6. ወላጅ/አሳዳጊ ወይም ሌላ ከወላጅ/ከአሳዳጊ በጽሁፍ የተወከለ አዋቂ ሰው ብቻ ቁጥጥር የሚደረግባቸውን የመድኃኒት ንጥረ ነገሮች ከትምህርት ቤቱ መረከብ/መውሰድ ይችላሉ።

7. በወላጅ/አሳዳጊ ወይም በተወከለ አዋቂ ሰው ያልተወሰዱ መድሃኒቶች DHHS በደነገገው ሂደት መሰረት ይወገዳሉ።

**ተዛማጅ ምንጮች፡-** Annotated Code of Maryland, Education Article, §7-401, §7-421, §7-426, §7-426.1, §7-426.2, and §7-446, and Health-General Article, §21-221(a); Code of Maryland Regulations, 10.13.12.01.B(1), 10.27.11.01-.02, 10.27.09.03I, and 13A.05.05.08F; Guidelines for Emergency Care in Maryland Schools, 2nd Maryland Edition (Maryland State Department of Education, 2015); Delegation of Nursing Functions to Unlicensed Direct Care Providers in a School Setting: Maryland State School Health Services Guideline, Maryland State Department of Education and Maryland Department of Health (January 2006); Maryland State Department of Education and Maryland Medical Cannabis Commission, Guidelines for Public Schools Allowing the Administration of Medical Cannabis to Students

**የደንቡ ታሪክ፡-** የደንብ ቁጥር 525-13፣ ኦክቶበር 1982 ተሻሽሏል፣ ጁን 8 ቀን 1992 ተሸሯል፤ ዲሴምበር 6 ቀን 2005 እንደገና ክለሳ ተደርጎበታል። ኤፕሪል 20, 2016 ተሻሽሏል፣ ኤፕሪል 27፣ 2023 ተሻሽሏል።

# የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የፀረ-መድሎአዊነት መግለጫ

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) በዘር ሐረግ፣ በጎሣ፣ በቀለም፣ በትውልድ ሐረግ፣ በዜግነት፣ በሃይማኖት፣ በስደት ሁኔታ፣ በጾታ፣ በጾታ መገለጫ፣ በጾታ ማንነት፣በጾታዊ ዝንባሌ፣በቤተሰብ መዋቅር/የወላጅነት ሁኔታ፣ በትዳር ሁኔታ ላይ የተመሰረተ ሕገወጥ አድልዎ ይከለክላል። ዕድሜ፣ ችሎታ (የግንዛቤ፣ ማህበራዊ/ስሜታዊ እና አካላዊ)፣ ድህነት እና ማህበራዊ-ኢኮኖሚያዊ ደረጃ፣ ቋንቋ፣ ወይም ሌላ በህግ ወይም በህገ-መንግሥት ጥበቃ የተደረገላቸው ወይም ትስስር ያላቸው ባህሪያት ላይ የሚደረግ ማናቸውንም ሕገወጥ አድልዎ ይከለክላል። መድሎ ወይም አድሎአዊነት፤ ሕብረተሰባችን ለረዥም ጊዜ እኩልነት፣ ፍትሕ፣ አብሮነት፣ ሁሉን አቀፍነትን፣ ለመፍጠርና ለማሳደግ/ለመንከባከብ ሲደረግ የቆየ ጥረትን  ይሸረሽራል/ያበላሻል። ቦርዱ ጥላቻን የሚያራምዱ ቋንቋን እና/ወይም ምስሎችን እንዲሁም ምልክቶችን መጠቀምን ይከለክላል፥ በተለይም በትምህርት ቤት ወይም በዲስትሪክት ሥራ ወይም እንቅስቃሴ ላይ ከፍተኛ ማደናቀፍ ሊያስከትል የሚችል ድርጊት-እንቅስቃሴ የተከለከለ ነው። የበለጠ መረጃ ለማግኘት፣ እባክዎ የሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ ፖሊሲ "Montgomery County Board of Education Policy ACA" ይመልከቱ፡- ከአድሎአዊነት ነጻ የሆነ ፍትሃዊነት፥ ሚዛናዊነት፥ እና የዳበረ ባህል "Nondiscrimination, Equity, and Cultural Proficiency"። ይህ መመርያ እያንዳንዱ ተማሪ ትኩረት የሚሻ መሆኑ(ኗ)ን  እና በተለይም የትምህርት ውጤቶች በምንም አይነት በግለሰብ ትክክለኛ ወይም ይሆናል ተብሎ በሚገመት ግላዊ ባህርያት የሚተነበይ እንደማይሆን የቦርዱን እምነት ያረጋግጣል። ፖሊሲው በተጨማሪም ፍትህ/እኩልነትን/ሚዛናዊነትን የሚያዛቡ ነገሮችን ለይቶ በማወቅ በቅድሚያ መወሰድ ያለባቸው እርምጃዎችን፥ የተዛባ ስውር አመለካከትን፣ ጭፍን/መሠረተ-ቢስ ልዩነት ማድረግን፣ በተቋማት የሚፈጸሙ መዋቅራዊ መሰናክሎችን፣ በትምህርት እና በሥራ ላይ እኩልነት እንዳይኖር ተፅእኖ የሚያደርጉ አሠራሮችን የሚገታ/የሚፃረር መሆኑን ያስገነዝባል። MCPS ለወንድ/ሴት ልጅ ስካውት እና ለሌሎች የወጣት ቡድኖች እኩል ተደራሽነት ይሰጣል።**

<table>
<tr><td>MCPS ተማሪዎች ላይ አድልዎ ሲፈጸም ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ*</td><td>MCPS ሰራተኛ ላይ መድሎዎ ሲፈፀም ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ*</td></tr>
<tr><td>Director of Student Welfare and Compliance<br>Office of District Operations<br>Student Welfare and Compliance<br>850 Hungerford Drive, Room 55, Rockville, MD 20850<br>240-740-3215<br>SWC@mcpsmd.org</td><td>Human Resource Compliance Officer<br>Office of Human Resources and Development<br>Department of Compliance and Investigations<br>45 West Gude Drive, Suite 2500, Rockville, MD 20850<br>240-740-2888<br>DCI@mcpsmd.org</td></tr>
<tr><td>በ1973 የተሃድሶ ህግ ሰክሽን 504 መሠረት ለተማሪ የአኮሞዴሽን/ መገልገያ ጥያቄ</td><td>በአካል ጉዳተኛ አሜሪካውያን ህግ መሠረት ለሰራተኞች የአኮሞዴሽን/ መገልገያ ጥያቄ</td></tr>
<tr><td>Section 504 Coordinator<br>Office of School Support and Well-being<br>Office of Well-being, Learning and Achievement<br>850 Hungerford Drive, Room 257, Rockville, MD 20850<br>240-740-5630<br>504@mcpsmd.org</td><td>ADA Compliance Coordinator<br>Office of Human Resources and Development<br>Department of Compliance and Investigations<br>45 West Gude Drive, Suite 2500, Rockville, MD 20850<br>240-740-2888<br>DCI@mcpsmd.org</td></tr>
<tr><td colspan="2">"Title IX" ድንጋጌ መሠረት፥ ስለ ጾታዊ መድሎአዊነት በተማሪዎች ወይም በሠራተኞች* ላይ ስለሚፈጸምባቸው ጾታዊ ጥቃቶች ጭምር ለሚቀርቡ ጥያቄዎች ወይም ቅሬታዎች</td></tr>
<tr><td colspan="2">Title IX Coordinator<br>Office of District Operations<br>Student Welfare and Compliance<br>850 Hungerford Drive, Room 55, Rockville, MD 20850<br>240-740-3215<br>TitleIX@mcpsmd.org</td></tr>
</table>

**ስለ መድሎአዊነት ቅሬታ/አቤቱታ ከዚህ ቀጥሎ ለተዘረዘሩት ሌሎች ኤጀንሲዎችም ማቅረብ ይቻላል፡-  U.S. Equal Employment Opportunity Commission (EEOC), Baltimore Field Office, GH Fallon Federal Building, 31 Hopkins Plaza, Suite 1432, Baltimore, MD 21201, 1-800-669-4000, 1-800-669-6820 (TTY);  Maryland Commission on Civil Rights (MCCR), William Donald Schaefer Tower, 6 Saint Paul Street, Suite 900, Baltimore, MD 21202, 410-767-8600, 1-800-637-6247, mccr@maryland.gov; or U.S. Department of Education, Office for Civil Rights (OCR), The Wanamaker Building, 100 Penn Square East, Suite 515, Philadelphia, PA 19107, 1-800-421-3481, 1-800-877-8339 (TDD), OCR@ed.gov, or www2.ed.gov/about/offices/list/ocr/complaintintro.html.

**ይህ ማስታወቂያ ከተሻሻለው የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ህግ ጋር የተሳለጠ ነው።

ይህንን ሠነድ ከእንግሊዝኛ ቋንቋ በተጨማሪ  በአማራጭ ቅርጸት ለማግኘት ከተጠየቀ፥ በ "Americans with Disabilities Act" ድንጋጌ መሠረት፣ MCPS Office of Communications በስልክ ቁጥር፡- 240-740-2837፣ 1-800-735-2258 (Maryland Relay)፣ ወይም PIO@mcpsmd.orgበመጠየቅ ማግኘት ይቻላል። የምልክት ቋንቋ ወይም ንግግር ትርጉም የሚያስፈልጋቸው ግለሰቦች  የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ የትርጉም አገልግሎት ጽ/ቤት በዚህ ኤሜይል ወይም ስልክ መጠየቅ ይችላሉ። MCPS Office of Interpreting Services at 240-740-1800, 301-637-2958 (VP) mcpsinterpretingservices@mcpsmd.org, or MCPSInterpretingServices@mcpsmd.org